# ለጥፋት አደግድጐ የተነሳ ጋዜጣ ሁሌ እንደሠጋ ሊኖር ግድ ይለዋል

አለ. አባዳማ /የጮሬሳው/ abaydagi@yahoo.com

ሚዲያ ለአንድ አገር ዴሞክራሲ ማበብና መጠናከር የሚጫወተው ሚና ከፍተኛ የመሆኑን ያህል ሙያና ስነ - ምግባርን እስካላከበረ ድረስ የሚያስከትለው አደጋ ምን ያህል የከፋ እንደሚሆን በንድፈ - ሃሳብ ብቻ ሳይሆን በተግባርም የተረጋገጠ ሐቅ ነው፡፡ የሚያስከትለው አደጋ በዴሞክራሲና በልማት ላይ ብቻ ሳይሆን በአገርና በሕዝቦች ሉአላዊነት ላይ ጭምር እንደሆነ በሩዋንዳ የተከሰተውን የዘር ማጥፋት ወንጀል ማስታወሱ ይበቃል፡፡

በአገራችን የነፃ ፕሬስ መታወጅን ተከትሎ በየሣምንቱ በመቶዎች የሚቆጠሩ የፕሬስ ውጤቶች ለገበያ ይቀርቡበት የነበረውን የ1980ዎቹን አጋማሽ እናስታውሳለን፡፡ ወደ ኋላ ሄድ ብለን የያኔውን ታሪክ ስንመለከት አንዳንዶቹን ጋዜጦች እና መጽሔቶች ያዘጋጁና ያሰራጩ የነበሩት በልዩ ልዩ ምክንያት ከያኔው የማስታወቂያ ሚ/ር በግምገማ ተባረው የነበሩ ጋዜጠኞች ግንባር ቀደም ተዋናይ ነበሩ፡፡ ባለመታደል እነዚያ ጋዜጠኞች በቂም በቀል ተነሳስተው የተከሉት የጥላቻ ሚዲያ እንደ ጠንካራ ተሞክሮ እየተወሰደ በሌሎች ጋዜጦችም ላይ ሰፊ ተጽእኖ ከማሳደሩ የተነሳ ብዙዎቹ ሚዲያዎች ከመንግሥት ጋር እሰጥ አገባ የሚገቡበት ጊዜ ብዙ እንደነበር ይታወሳል፡፡ የአብዛኞቹ ጋዜጦች ምንነት በጊዜ ሂደት እየጠራ ሲመጣ አንዳንዶቹ እየተንገዋለሉ ሲወድቁ አንዳንዶቹ ደግሞ በአንባቢ እጦት እየተዘጉ የሄዱበት ሁኔታ የነበረ ሲሆን አንዳንዶቹም አለቅጥ ሕግን ተላልፈው ሲገኙ እንዲዘጉ የተደረጉበት ጊዜም ነበር፡፡

ሆኖም አሁን መሻሻል የሚታይበት ሁኔታ ቢኖርም አሁንም መለወጥ ያቃታቸው አንድ ወይም ሁለት የፕሬስ ውጤቶች ግን አልታጡም፡፡ የጽሑፌ አነሳስ ለዚህች አገር ሰላም፣ ዴሞክራሲና ልማት ብቻ ሳይሆን ለህልውናዋም ጭምር አደገኛ ሆኖ

ስላገኘሁት አንድ ‹‹የግል›› ጋዜጣ ለመተቸት ሲሆን ይህንንም ያደረግሁት ኃላፊነት እንደሚሰማው ዜጋ ሆኜ የታዘብኩትን ለአንባቢያን ለማካፈል ብቻ ሳይሆን ጋዜጣው ድክመቶቹን አርሞ አንደ አንድ ትክክለኛ ሚዲያ ለቀና አላማ እንዲቆም፣ አሻፈረኝ ካለም የሚመለከተው አካል የከፋ ነገር ከመድረሱ በፊት ፈር እንዲያሲይዘው የጠበቀ አደራዬን ለማስተላለፍ ነው፡፡እዚህ ላይ አንባቢያን እንዲረዱኝ የምፈልገው ጋዜጣው ለቀና ዓላማ ይቁም ስል መንግሥትን መተቸቱን ያቁም ለማለት እንዳልሆነ ነው፡፡ይልቁንም በማስረጃ ላይ ተደግፎ የሚደረግ ትችት ፈርጀ ብዙ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ ሊበረታታ የሚገባው እንጂ የሚኮነን ተግባር አይደለም፡፡ በሃሰት ላይ ተመሥርቶ የሚደረግ ትችት ግን አፍራሽነቱ የጐላ በመሆኑ ሃይ ሊባል ይገባዋል ነው - የኔ አስተያየት፡፡

የጽሁፌ ትኩረት የሆነውን ‹‹ አዲስ ነገር ›› የተባለውን ጋዜጣ ለመተቸት ስነሳ የጋዜጣውን ቋሚ አምደኞች በፎቶ አስደግፎ ማቅረቡ ማለፊያ አሰራር በመሆኑ ያስመሰግኑታል፡፡

ከላይ የጠቀስኳቸው ጠንካራ ጐኖቹ ጉልህ የምላቸው ሲሆኑ ሁሉም ቢሆኑ በአቀራረብ ላይ ያጠነጠኑ ናቸው፡፡ ወደ ደካማ ጐኑ ስመለስ በቀዳሚነት የሚታየውና ማንም የጋዜጠኝነትን ሀሁ የቀመሰ አይቶ የማያልፈው ድክመቱ ጭብጥና የግል አስተያየትን እያደበላለቀ ማቅረቡ (opinionated) መሆኑ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ከይዘት ጋር የተያያዘ ከመሆኑ አኳያ ሚዛን የሚደፋ ድክመት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

እንደሚታወቀው በጋዜጠኝነት ሙያ ጭብጥ የሚባለው አንድ ጋዜጠኛ በትክክል የሆነን፣ የተደረገን፣ የተባለን ነገር እንዳች ነገር ከራሱ ሳይጨምር ሳይቀንስ የሚያቀርበው ዘገባ ነው፡፡ ለዚህም ነው፡፡ ጋዜጠኛ ሕዝብ በኮንትራት የቀጠረው የሕዝብ አይንና ጆሮ ነው የሚባለው፡፡ ጋዜጠኛው የቱን ያህል የራሱ ፍላጐት በጉዳዩ ላይ ቢኖረው - በምንም መልኩ ትንሽ እንኳን ቢሆን የራሱን ፍላጐት ሊጨምርበት ሙያው አይፈቅድለትም፡፡ ጋዜጣን ዋነኛ የመረጃ ምንጭ የሚያደርገውም ይኼው ባህሪው ነው፡፡ ጋዜጠኛውስ እንደአንባቢው ሁሉ የራሱ

ፍላጐት አይኖረውም ወይ? ፍላጐቱንስ እንዴት ያደርገዋል የሚል ጥያቄ መነሳቱ አይቀርም፡፡ መቼም ታፍኖ ይሙት አይባልምና ለዚህ የሙያው አባቶች የጠራ መፍትሄ አስቀምጠውለታል፡፡ ይኸውም እንደ ጋዜጠኛ ሃሳቡን የሚተነፍስበት ማንም የማይጋራው « ኤዲቶሪያል» የተባለ አምድ አለ፡፡ ኤዲቶሪያል - የብዙ ኤዲተሮች የጋራ አቋም እንደመሆኑ ሃሳቡ በኤዲቶሪያል እንዲስተናገድ ይደረጋል፡፡አልፎ አልፎም በአንድ አዘጋጅ ስም እንዲወጣም ይደረጋል፡፡ ጋዜጦች እንደማንኛውም አንባቢ አስተያየቱን የሚሰጥበት «የአስተያዬት» አምድን ተጠቅሞ የግል አመለካከቱን ለሕዝብ ከማድረስ የሚከለክለው የለም፡፡ ( እኔ አሁን ሃሳቤን እንደአንድ ዜጋ እንድገልጽ ያስቻለኝ የአዲስ ዘመኑ « አጀንዳ » አምድ ከዚህ እውነታ በመነሳት መሆኑን ልብ ይሏል፡፡)

በዚህ መሠረት ጋዜጦች ከዜና ፍሬ ነገር ዘገባቸው በተጨማሪ የተለያዩ አስተያዬቶችና ሃሳቦችን በተለይ የሚያስተናግዱባቸው ገፆችንም ይመድባሉ፡፡ በተለመደው አሠራር የገፁን ግራ ክፍል ለኤዲቶሪያል፣ የቀኙን ክፍል ለአንባቢያን አስተያየት ( ኦፒኒየን) ብለው የሚመድቡት ሲሆን የዚህ ገጽ ስያሜ በእንግሊዝኛው አጠራር « ኦፕ - ኤድ » ይባላል - ከርእሰ አንቀፁ ጋር ትይዩ የሆነ opposite to the editorial ማለት ነው ፡፡ የጋዜጠኝነት ሙያ በዳበረባቸው የዓለም ክፍሎች አንባቢያን ( ከሙያው ውጪ ያሉትን ጨምሮ ) ይህንን እውነታ ጠንቅቀው ስለሚያውቁት ከኦፕ - ኤድ ገጽ ውጪ ያሉት የዜና ትረካዎች ሁሉ ከዘጋቢው የግል አስተያዬት የፀዱ የእውነታው ነፀብራቆች ናቸው ብለው ይቀበላሉ፡፡ በኤዲቶሪያል አምድ ላይ የቀረበ ደግሞ የጋዜጣው አዘጋጆች የግል ወይም የቡድን አስተያየቶች፣ በኦፒኒየን ላይ የሰፈረው ደግሞ የግለሰቦች አስተያየቶች መሆናቸውን በውል ለይተው ስለሚያውቁና አስተያየት እንደ ፍሬ ነገር ዘገባ ሳይሆን በባህሪው እውነት ወይንም ሃሰት ሊባል የማይችል እሴታዊ ብያኔ ( value Judgment) በመሆኑ የተሳሳቱ ትክክለኛ ምክንያታዊ ይዘት ይበሏቸው እንጅ እውነት ናቸው ብለው አይወስዷቸውም፡፡

በሙያው በኩል ስላለው ተጨባጭ ሁኔታ ይህን ያህል ካልኩ « አዲስ ነገር » እንዴት እየሰራ እንደሆነ ጥቂት ለመመልከት እንሞክር፡፡ ጋዜጣውን አልፎ አልፎ

ለማየት ባደረግሁት ሙከራ ከመጀመሪያ ገፅ አንስቶ እስከመጨረሻው ድረስ የፍሬ ነገር ዘገባና አስተያየትን እያላቀጠና እያቀላቀለ የመሄድ ክፉኛ አባዜ የተጠናወተው ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡ በእርግጥ የንባብ ባህሉ እምብዛም ባልዳበረበት በእኛ አገር ተጨባጭ ሁኔታ ችግሩን ነጥሎ ሊያየው የሚችል በርካታ አንባቢ አይኖርም ማለት ይቻል ይሆናል ፡፡ ችግሩን አሳሳቢ የሚያደርገውም ለዚህ ነው፡፡ አንባቢው የፍሬ ነገር ዘገባና አስተያየትን ለመለየት የማይችልበት አሳሳች አቀራረብ እንዲህ ተደበላልቆ የሚቀርብለትን መረጃ እንደ ፍሬነገር በመውሰድ ስህተት ላይ የመውደቁ አጋጣሚ ሠፊ ነው፡፡ በበኩሌ ጋዜጣው ለሚታይበት ለዚህ ጉልህ ድክመት የማስቀምጠው ሁለት ግምቶችን ነው፡፡ አንደኛው ግምቴ የሙያ እውቀቱና ክህሎቱ የሌላቸው ግለሰቦች በአገሪቱ ሕገ - መንግስት የተረጋገጠላቸውን የመናገርና የመፃፍ መብት ተጠቅመው ወደ ሥራው ሲገቡ ሙያው ስለሚጐድላቸው ባለማወቅ የፈፀሙት ስህተት ሊሆን ይችላል የሚል ነው፡፡ እንደእኔ ይኼኛው ምክንያት ትክክለኛ ቢሆን እመርጣለሁ፡፡ ካልሆነ ግን የሙያ ችግር ሳይኖርባቸው በራስ ጥቅም ታውረው ሆን ብለው ከጋዜጠኝነት መርህ የተቃረነ አሠራር መከተልን መርጠዋል የሚል ነው - ሁለተኛው ግምቴ፡፡ ይህ ነው ከምንም በላይ የሚያሳስበኝ፡፡

ጋዜጣው በፊቸር መልክ ሰፋ ያለ ሃተታን ሲመርጥ ፀሃፊው (ዎቹ ) የግል አስተያየታቸውን እንደፈለጉ እንዲደረድሩ ልዩ ፈቃድ የተሰጣቸው መስለው ነው የሚታዩት፡፡የጋዜጣው አምዶች ከተገቢው በላይ በአንድ አገር ጥቅሶች የተሞሉ መሆናቸው የየአምደኞቹ ከራሳቸው ምክንያታዊና ፍሬ ነገራዊ ትንተናዎች ይልቅ "በታዋቂ" ምሁራን ጋሻ "በእገሌ እንዳለው" የክርክር ሽፍጥ "logical fallacy" ለማለፍ መሞከር አይነተኛ ባህሪያቸው መሆኑን መገንዘብ አያዳግተውም ፡፡ አንዳንዴ አዋቂ ለመምሰል በሚደረግ ሙከራ እንግሊዝኛ ቃል ጣል ማድረግ በ ‹‹አዲስ ነገር ›› የተለመደ ሲሆን አንዳንዴ የግል አስተያየት እንዳይመስልባቸው አልፎ አልፎ የባህር ማዶ ፀሐፊዎችን አንዳንዴ በሥም አንዳንዴ ካለሥም አሊያም በደፈናው አንድ የፖለቲካ ምሁር ፣ የህግ ምሁር፣ ታዛቢዎች ወዘተ የሚሉ ኃረጐችን በመቀጠል ብቻ እውነት ለማስመሰል ይሞክራሉ፡፡ ከጋዜጣ ሙያ አንፃር አንዳች ዋጋ የማይሠጠውን የአንድን ጋዜጠኛ የግል አስተያየት በምሁራን፣ በዲፐሎማቶች፣

በውጪ ዜጎች ሥም ጀቡኖ ለማቅረብ የሚደግ ጥረት የመረጃ ጥራት ድክመትን እንጂ ጥንካሬን አያሳይም፡፡ ይሁንና ይህ ዘዴ የሙያው እውቀት በሌለው ሕዝብ ዘንድ የሚፈጥረው ተጽእኖ ቀላል አይደለም፡፡ አደጋው ያለውም እዚህ ላይ በመሆኑ ጋዜጣው ሊስተካከል አሊያም ሊታረም ይገባዋል የምለው ከዚህ በመነሳት ነው፡፡ አመጽና ሁከትን ለመቀስቀስ የሚጠቅምን የፕሮፖጋንዳ ቴክኒክ ተጠቅሞ ሕዝብን ለማወናበድና ለማነሳሳት የሚደረግ ጥረት በአገርና ሕዝብ ላይ ነፍጥ አንስቶ ከመውጋት ወይም የሽብር ጥቃት ከማድረስ ቢበልጥ እንጂ የሚተናነስ አይደለም፡፡ ‹‹ከአንድ ሺህ ጦር አንድ ወሬኛ የፈታው›› የሚባለው ለዚህ ነው፡፡

ለዚህ አባባሌ ማስረጃዎችን ማቅረብ ግድ ይለኛል እና በ16/01/02 የቀረበውን እትም እንመልከት፡፡ ገና በፊት ገጹ ፎቶራፍ በሚያህል ፎንት ‹‹ 10ሩ የምርጫ 2002 ስጋቶች ›› በሚል መሪ ርዕስ ያስቀመጠው ዘገባ በገጽ 2-3 ላይ ፊቸር ተብሎ ሠፍሮ እናገኘዋለን፡፡ ጽሁፉን እንደስከዛሬው በአንድ ፀሐፊ ሥም ለመሰየም አልደፈረም፡፡ ኃላፊነቱን ለጋዜጣው ‹‹ የፊቸር ሪሰርች ቡድን›› ከሰጠ በኋላ ወደሃተታው ሲገባ ሕዝቡ ምርጫ 2002ን በጉጉት መጠባበቁን አስመልክቶ ሲገልጽ ሳይኮሎጂስቶች ‹‹ዴዣቡ›› ይሉታል የሚል አንድ የእንግሊዝኛ ቃል ይደነቅራል፡፡ የሚያሳዝነው ቃሉ ከጉዳዩ ጋር የማይዛመድ መሆኑ ነው፡፡ “Jamais vu” ትክክለኛ አነባበቡ ‹‹ ዠሜቩ›› ሲሆን የሚገልፀው ጽንሰ ሃሳብ ዘወትር የሚታወቅ አንድ ነገር በግለሰብ አእምሮ ውስጥ እንደአዲስ ድቅን እያለ በማስታወስ ችሎታው ላይ የሚፈጠር መታወክን ነው፡፡ ሕዝብ በሰከነ አእምሮው በየአምስት አመቱ በጉጉት የሚጠብቀውን ምርጫን ያህል ነገር ጋዜጠኛው(ዎቹ) ለማጣጣል ስለፈለጉ ብቻ ከስካርና እብደት ጋር ማያያዙ የግል ምኞትን እንጂ እውነታን አያመላክትም፡፡ ለዚህ ዋቢ የሚሆነው ጋዜጣው ራሱ ሃተታውን ሲጀምር የተጠቀመበት አገላለጽ ሲሆን ‹‹በጋዜጦች ገፆች፣ በኤምባሲዎች ኮክቴሎች፣ በየቡና ቤቶችና ካፍቴሪያዎች ለሚደረጉ የፖለቲካ ውይይቶች እና እሰጥ አገባዎች ምርጫው የአፍ ማሟሻ እየሆነ ነው››በማለት መላው ሕዝብ መጪውን የምርጫ ጉዳይ ከምንም በፊት የአፍ ማሟሻ እንዳደረገው በገለፀበት አንደበቱ ይህ ‹‹ሕዝቡ ካሁን በፊት የተፈጠረውን እያወቀ እንዲህ መሆኑ ስካር ነው›› ሲሉ የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር መናገራቸውን ይገልጻል፡፡ ተናገሩ የተባሉት የካሊፎርኒያ ስቴት የፖለቲካ ሳይንስ ፕሮፌሰር በመሆናቸው

ለጉዳዩ ክብደት መስጠታችን አይቀርም፡፡ ይሁንና በሥም የተጠቀሱት ፕሮፌሰር ይህንን መቼ፣ የት ነው ያሉት? የሚለውን ጋዜጣው ሆን ብሎ በመደበቁ እውነታውን እንዳንረዳ አድርጎናል፡፡ እውነታውን በበኩሌ ሳጣራ ያረጋገጥሁት ፕሮፌሰሩ የአንድ ተቃዋሚ ፖለቲካ ድርጅት አባል/ደጋፊ ሲሆኑ  ንግግሩንም ያደረጉት በቅርቡ አሜሪካ ውስጥ በተደረገ የተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲ ስብሰባ ላይ ነበር፡፡ በመሆኑም የእሳቸውን ንግግር ከአንድ ገለልተኛ የፖለቲካ ምሁር የተገኘ መረጃ ለማስመሰል መሞከር በጋዜጠኝነት ሙያ ላይ የተፈፀመ ሸፍጥ ነው፡፡

‹‹አዲስ ነገር›› በዚህ ብቻ አያቆምም ፡፡ ‹‹ፋሽን ነው፤ ውጤቱን እያወቅነው እንኳ የዚህ ፋሽን ወረት እንዳያመልጠን እንፈልጋለን›› ሲሉ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ጥናት የሚያደርጉ አንድ ሌላ ምሁር መናገራቸውንም ያክላል፡፡ ስለምሁሩ ምንነት፣ መቼ፣ የትና እንዴት አሉት? ለመሳሰሉት ቁልፍ ጉዳዮች ፍንጭ ባለመስጠቱ ማረጋገጥም፣ ማስተባበልም አይቻልም፡፡

ከምርጫው ጋር ተያይዞ የብሔረሰቦች ግጭት ሊከሰት እንደሚችል ‹‹አንድ የዩኒቨርሲቲ ምሁር›› ተናገሩ ከማለት ውጭ ማስረጃ ያጣለትን ጉዳይ ሲያብራራ ግንቦት 7፣ ኦነግ እና ኦብነግ ‹‹በአገር ውስጥም ይሁን ከአገር ውጪ በርካታ ደጋፊዎች ያላቸው የፖለቲካ ቡድኖች ናቸው›› በማለት በአሸባሪነትና ንፁሃንን በመግደላቸው የተነሳ ሕዝብ አንቅሮ የተፋቸው ፀረ-ሰላም ቡድኖች በርካታ ደጋፊዎች ያላቸው መሆናቸውን ስላሳወቀን ጋዜጣውን እናመሰግነዋለን እንዳንል የሚያቀርብልን አሃዝ ወይም መረጃ የለም፡፡ እነዚህ ቡድኖች ምን ዓላማ ይዘው እንደሚንቀሳቀሱ የደህንነት ባለሙያዎች ተናገሩ ሲለንም ተናገሩ የተባሉት  እነዚህ ኤክስፐርቶች የፀረ - ሽብር  ግብረ- ኃይሉ ወይስ የእነኦነግ ስለመሆናቸው የገለፀው የለም፡፡በግላጭ በህገወጥ የወንጀል ድርጊት ተከሰው በገለልተኛው ፍርድ ቤት ተፈርዶባቸውና ጥፋታቸውን ተናዘው ንስሃ ገብተው በቅድመ ሁኔታ ላይ በተመሰረተ ይቅርታ የተፈቱትን እንደሰማእታን ሲያቀርቡልን የከረሙት አዲስ ነገሮች ለአሸባሪ ድርጅቶች ድጋፍና ቅስቀሳ ማካሄዱን በይፋ ተያይዘውታል፡፡ እነ ኦነግና ፣ግንቦት ሰባትን መሰል አሸባሪዎች የኢትዮጵያ ህዘብ ድጋፍ

ከበስተጀርባቸው እንዳለ አድርጎ ማቅረብና መሪዎቹን ታላቅ ሰው አድርጎ መኳኳል ጋዜጣው ከወንጀል ጋር የጀመረውን አጉል ድሪያ በግልፅ አመላካች ነው ፡፡

ጋዜጣው አልፎ ተርፎ በመጪው ምርጫ የመራጮች ቁጥር አነስተኛ ሊሆን ይችላል በሚል ለማስረዳት ሲሞክር በዋቢነት የጠቀሰው ጄ. አቢንክ የተባሉ የሆላንድ የፖለቲካ ሶሲዮሎጂስትን ነው፡፡ እኚህ ሰው በእርግጥ በኔዘርላንድ የአፍሪካ ጉዳዮች ጥናት ማዕከል ተባባሪ ሆነው በማገልገል ላይ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ምሁሩ በምርጫ 97 ማግሥት ተፈጥሮ ከነበረው ሁኔታ ጋር አስታክከው የዛሬ አራት ዓመት ገደማ ባቀረቡት አንድ ጽሁፍ ላይ የአፍሪካ አገራት ወደ ዴሞክራሲ በሚያደርጉትሽግግር የሚያጋጥሟቸው ችግሮች ምን ያህል ስር የሰደዱ መሆናቸውን ገልፀው ነበር፡፡ እኚህ ሰው ‹‹በኢትዮጵያ በቅርብ ጊዜ ዴሞክራሲያዊ ፉክክር ያለበት ምርጫ አይደረግም›› የሚል ተስፋ መቁረጥ በሕዝቡ ላይ እንዳሳደረ ስለመናገራቸው ለማወቅ ብዙ ደክሜ አላገኘሁም፡፡ ጥቅሶቹን ከየስርቻው የሚለቃቅሙት አዲስ ነገሮች ለአንባብያን ያላቸውን ንቀትም የሚገልፁበት አንድ ስለት ይህ ነው ሰውዬው ይህን ይበሉም፤ አይበሉም ከቲዩሪ ይልቅ በተግባር የተረጋገጠው ሃቅ ከዚህ በተቃራኒ ነው፡፡ በ2000 ዓ.ም የተካሄደው የማሟያ ምርጫ በተግባር አረጋግጦታል፡፡

ጋዜጣው ጭብጥንና የግል አስተያየትን እያደበላለቀ የሚሄድ ለመሆኑ በአንድ ፊቸር ላይ ብቻ በርካታ ማስረጃዎችን ማቅረብ ይቻላል፡፡ የቦታ ውሱንነት ስላለ ሁሉንም መግለጽ አይቻልም፡፡ ችግሩ በፖለቲካ አምዱም የሚስተዋል ነው፡፡ በተለይም ‹‹ፎርፌ›› በሚለው አምዱ ላይ የምናገኘው ከሁሉ አሳፋሪ የሆነ ነገር ነው፡፡ የአዘጋጁም ሥም ይሁን ፎቶ አሊያም ስኬች ያልያዘው ይኸው - አምድ ከጋዜጠኝነት ባህርይ ውጪ ሙሉ በሙሉ በፈጠራ ላይ በተመሠረተ አሽሙር ስላቅና ሽሙጥ ዴሞክራሲያዊ አሰራሮችን ፣እሴቶችን ተቋማትንና መሪዎችን ለማንኳጠጫ የሚሞክርበት አምድ መሆኑ ግልጽ ነው - ለሙያተኛው፡፡ ሌላውን ሕዝብ ግን ምን ያህል እንደሚያሳስት ለመረዳት ካስፈለገ ከተተኪው ጠቅላይ ሚኒስትር ጋር በአምስተርዳም የሚገኝ ጋዜጠኛ ያደረገው ቃለ ምልልስ ብሎ በዚያው እትሙ ያቀረበውን የፈጠራ ጽሁፍ ማምንታዊው ‹‹ፕሬስ ዳይጀስት››

የተባለ የእንግሊዝኛ ዳይጀስት ጋዜጣ እንደ እውነት በመውሰድ በኦክቶበር 1,2009 እትሙ ላይ ቀጣዩ ጠ/ሚኒስትር ታወቁ በሚል ርእስ ተርጉሞ ማውጣቱን ልብ ይሏል፡፡

በመጨረሻም የጋዜጣው አስኳል ወደሆነው ርዕሰ አንቀጹ እንሂድ፡፡ በመሠረቱ ርዕሰ አንቀጽ አንድ ሚዲያ አቋሙን የሚያሳውቅበት፣ ለአገርና ለህዝብ የሚጠቅሙ ሃሳቦችን የሚያቀርብበት በመሆኑ በመንግስት፣ በፖሊሲ አውጪዎችና በተመራማሪዎች ጭምር ልዩ ትኩረት የሚሰጠው አምድ ነው፡፡አዲስ ነገር በልዩ ፍቅርና ቁርጠኝነት በልሳንነት ከሚያገለግላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች (መድረኮች ) ጋር የሚጋራው አንድ ትልቅ ስጋት እነዚህ ሃይሎች በቀጣዩ ምርጫ የረባ የህዝብ ድጋፍ ሊያገኙ የማይችሉ የመሆናቸውን እውነታ ነው፡፡ይህን ከውስጣዊ ድክመት የመነጨ ችግራቸውንም በምርጫ ሂደቱ ላይ በማላከክ ሚሚረትን መርጠዋል፡፡ ጋዜጣው በዚህ ረገድ ቀዳሚ ሚና ለመጫወት ሲሞክር ይታያል፡፡

ከዚህ አኳያ ይህን ደግሞ ደጋግሞ የሚወቅጠውን አቋሙን ለማስተጋባት የተጠቀመበትንና በተጠቀሰው እለት የቀረበውን የአዲስ ነገር ርዕሰ አንቀጽ ስንመለከት ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫውን በሕትመቱ ሰፊ ሽፋን በተሰጠው ምርጫ 2002 ላይ ማድረጉ ተገቢ ቢሆንም ከቅርጽና ከይዘት አኳያ ግን ስናየው የወረደ ሆኖ ነው የምናገኘው፡፡ ከቅርጽ አኳያ የመጀመሪያው አንቀጽ በገጽ 2 እና 3 ላይ ስለቀረበው ፊቸር ምንነትና ስለአዘጋጁ ማንነት ይነግረናል፡፡ይህ እጅግ አስቂኝ ነው፡፡ በማስከተል በሁለተኛው አንቀጽ ደግሞ ይኸው ፊቸር ስለተዘጋጀበት ዓላማ ነው የሚነግረን - በርዕሰ አንቀጽ ላይ! ከይዘት አኳያ ስናየው ደግሞ እንዲህ ይለናል ፡- ‹‹ የመጀመሪያ ጽሁፋችን ስለምርጫው ስጋቶች የሚያትት ቢሆንም ለችግሮቹ እንድንዘጋጅ እንጂ ምርጫውን የማጠልሸት ፍላጎት የለውም፡፡›› በማለት በሁለት ገጽ (ገጽ 2 እና 3) ሙሉ ጥላሸት ሲቀባ የዋለውን ሰፊ ዘገባ ዓላማ ገጽ 14 ላይ በሚገኘው ርዕሰ አንቀጽ ላይ በአንዲት መስመር ለማድበስበስ መሞከሩ - ያውም ርዕሰ አንቀጽ ላይ - እርግጥም አሳፋሪ ነው፡፡

እንግዲህ ርዕሰ አንቀጽ ሊባል የሚችለው የፅሁፉ አካል የሚጀምረው ከ3ኛው አንቀጽ ነው፡፡ ጋዜጣው ከሚያምንበት ሎጅክ ተነስቶ በርዕሰ አንቀጹ አቋሙን ማሳወቅ ሲገባው ያፈገፍጋል፡፡ ሚድያው ይፈራል፣ ተቃዋሚው ይፈራል ያለን ጋዜጣ መፍራታቸው ተገቢ ነው ወይስ አይደለም በሚለው ላይ የግዴታ አቋም መያዝ ነበረበት፡፡ ፍርሃቱ አለ ካለም ይወገድ ዘንድ ሃሳቡን ማንፀባረቅ በተገባው ነበር፡፡ ምርጫውን ተገን አድርገው እንደኦነግ፣ አብነግና ግንቦት 7 ጥቃት ሊያደርሱ ይችላሉ ብለናል እና በበኩሌ እነዚህ ፀረ - ሰላም ቡድኖች ከዚህ አይነት ተግባር ሊታቀቡ ይገባል ሲል መስማት እፈልጋለሁ፡፡ ሌላም ከሆነ አቋሙን ሊያሳውቀን ይገባል፡፡

ከዚያ ውጪ ርዕሰ አንቀጽን በሚያህል ክብደት በሚሰጠው ቦታ ላይ ገጽ ሁለትና ሦስት ላይ የተጻፈውን ፊቸር ያዘጋጀሁት እኔ ሳልሆን የፊቸር ቡድኑ ነው፣ ጽሁፉ የተዘጋጀበት ዓላማ ምርጫውን ለማጠልሸት አይደለም ማለት ራስን ከተጠያቂነት ማሸሽ እንጂ የገለልተኛ ጋዜጣ አቋም አይደለም፡፡

እዚህ ላይ ጋዜጣው ምርጫ 97ን ተከትሎ አመጽና ሁከትን በመቀስቀስ ዋነኛ ተዋናይ በነበሩት አንድ እና ሁለት ጋዜጠኞች ላይ የተወሰደውን አስተዳደራዊ እና ሕጋዊ እርምጃ በሁሉም የአገሪቱ ሚዲያዎች እና ጋዜጠኞች ላይ እንደተፈፀመ አስመስሎ በማቅረብ ከምርጫ 2002 ጋር በተያያዘም ሚዲያዎች ተመሣሣይ እርምጃ ይወስድብናል ብለው እንደሚሰጉ መግለፁ ራሱን ትዝብት ላይ የሚጥል ነው፡፡ በምርጫ 2002 ላይ አንደነዚያ ዓይነት ጋዜጠኞች እና ጋዜጦች መኖር እንደሌለባቸው የሚያምነው መንግስት ብቻ እንዳልሆነ ጠንቅቀው አውቀው ራሳቸውን ከተመሳሳይ የጥፋት ተግባር ሊያቅቡ እንደሚገባቸው ማስጠንቀቂያ ጭምር ስለሆነ አሁንም ደግመው ደጋግመው ሊያስቡት ይገባል እላለሁ፡፡ እንደ እውነቱ ከሆነ የእነዚህ የወንጀል ልሳን የሆኑ ጋዜጦች መወገድ ለዴሞክራሲያችን ማበብ ከፍተኛ ሚና እንደሚጫወት ሁሉም ይገነዘበዋል፡፡መንግሥትም የነፃ ፕሬስን መብት በማክበሩ ነው አዲስ ነገርን መሰል ፅንፈኛ ጋዜጣ ጨምሮ ሁሉም ጋዜጦች ሕልውናቸው ተከብሮላቸውና ሕጋዊ ጥበቃ ተደርጐላቸው ያሻቸውን እያሉ የሚገኙት፡፡ ለተቃዋሚ ፓርቲዎች ወግነዋል በሚል ምክንያት እያሳደደ

የሚያጠቃቸው ቢሆን ኖሮ ዛሬ አንድም ‹‹የግል›› ጋዜጣ በይበልጥም አዲስ ነገርን መሰል ፅንፈኛ ለተቃዋሚ ቡድኖች በልሳንነት የሚያገለግል ጋዜጣ ባልኖረ ነበር፡፡ የጋዜጠኝነት ጭምብል አጥልቆ አገርን ለብጥብጥ እና ለሁከት መዳረግ ተራ ወንጀለኛነት ስለሆነ የአገርም፣ የሕዝብም ጠላት ነውና አይቀጡ ቅጣት ይገባዋል፡፡ በዚህ ላይ ከቶ ማመንታቱ አብቅቶ መንግሥት በሁነኛ መረጃ ላይ የተመሠረተ ጥፋት ሲከሰት ሕዝብና አገር የሰጠውን አደራ በአግባቡ መወጣት ይገባዋል ባይ ነኝ፡፡

በዘዴ ሚዲያና የፖለቲካ ፓርቲዎች አመጽ እንዲያነሳሱ፣ ሕዝቡ እንዳይመርጥ ወዘተ መቀስቀስ ወንጀል ነውና ይህን የሚፈጽም ሕገ - ወጥ ሚዲያ ሁሌ እንደሰጋ ቢኖር አያስደንቅም፡፡ በበኩሌ ግን ምርጫው ሳይጀመር ምርጫውን ለማወክ የሚደረግ አንዳች እንቅስቃሴ መገታት ያለበት ምርጫው ሲደርስ ወይም ካበቃ በኋላ መሆን እንደሌለበት ከትናንቱ ልንማረው የሚገባ ታላቅ መልዕክት ነው እላለሁ፡፡